

# መለስና
# የእስከወዲያኛው እረፍት

ተስፋዬ ዘነበ (ኖርዌይ በርገን) 22-08-2012

ላለፉት ሃያ አንድ አመታት በኢትዮጲያ ውስጥ ለተገነባው እጅግ አምባገነን ሰርዓት የጀርባ አጥንት የነበረ ዘረኛው መለሰ ዜናዊ በየቀኑ ከማይጠፋበት ሁሌ ውሸት ብቻ ከሚነገርበት የቴሌቪዥን መስኮት መሰወሩ አነጋጋሪ ሆኖ ላለፉት ሁለት ወራት ከቆየ በኋላ እንሆ እልባት አግኝቷል ፡፡G20 ስብሰባ ሜክሲኮ ላይ ከታየ ወዲያ ለወራት  የተሰወረውን አምባገነን! ከህውሃት ሰወች የህክምና እረፍት ላይ እንዳለ ቢነገርም በሌላ ወገን ዘረኛው መለስ ዜናዊ ከነ ክፉ ስራው ይቺን አለም መሰናብቷል የሚለው በስፋት ተነግሮ ነበር፡፡

የሚገርመው የዚህ ህኩይ ስርዓት ባልደረቦች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እየወጡ የሚሰጡት የተለያየ እና የተምታታ  መግለጫ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነባቸው ባንዳዎች ባገኙት አጋጣሚ የእውር ድንብራቸውን የሚዘላበዱት ጥቂት ደጋፊዎቻቸውን ለማረጋጋት እንጂ በዙሃኑ ሕዝብ ከቁብ እንደማይቆጥራቸው ስተውት አይደለም፡፡ የሚደግፉትና የሚደነፉለት ድርጅት ሚስጥር ደብቆ ብርታቱንና ድፍረቱን ሰልቧቸው በተመሳሳይ ጨለማ ውስጥ እንዳሉ ማስተዋል ያቃታቸው ሆድ አደሮች በግትር አቋማቸው ፀንተው የመሪያቸው እስትንፋስ ለወራት የመጥፋቱን ሚስጢር አለቆቻቸው የሚያቀርቡላቸው የተዛባ ዲስኩር አምነው እያስተጋቡ ነበር፡፡

መለስ ተሸሎት ወይም አገግሞ አይነሳም፡፡ ሞቷልና፡፡ ሚስጢር መጠበቅ የወያኔ ስልት ወይም ባህል ነው የሚሉን ሁሉ አሁንም አስተሳሰባቸው ከደደቢት ያለዘለለ ካልሆነም ሃያ አንድ አመት ረግጠው የገዙትን ሕዝብ ንቀት እንጂ እውነታን አያሳይም፡፡ የመለስ ሞት ግልግል ነው፡፡ በአንፃራዊነት ከሌሎች ጭፍሮቹ በተለየ በክፋት የተካነ ነው፡፡ ለሰብዓዊ ፍጡር ክብር የለውም፣ ሕዝብ ያከበራቸውን በማዋረድ አና በማሳጣት ይደሰታል፣ ለስልጣኑ ስለሚፈራ በሃሳብ የሚበልጡትን ሁሉ ይገላል ያሳድዳል፣ ካልበላሁ እበትነዋለሁ ያለችው ዶሮ አይነት ስለሆነ ከሱ በኋላ ስለሚኖረው አገር እና \ህዝብ ደንታ አልነበረውም፣ ብቻ መለስ በየትኛውም መለኪያ ቅን ልቦና የሌለው ፍፁም ከፉ የኢትዮጲያ ጠላት ነበር፡፡

ሃያ አንድ አመታት የስልጣን ዘመኑ መለስ በሚችለው ሁሉ እኩይ ምግባሩን  ተጠቅሞ ኢትዮጲያንና ኢትዮጲያዊያንን ለማጥፋት አቅሙ የፈቀደውን አድርጓል ፡፡የብዙ ታሪክ ባለቤት የሆነች ኢትዮጲያን የምታክል  አገር መሪ፣ መሪ ሆኖ እራሱን በድርጅትና በዘር ማህቀፍ ውስጥ ያስቀመጠ፣ ለአገር እና ህዝብ ክብር የሌለው፣ ለዘመናት በብዙ መስዋህትነት የተከበረ ዳር ድንበርዋን አሳልፎ ለባእዳን የሸጠና በዳረጎት የሰጠ፣ ሰንደቃችንን ያዋረደና በተራ ጨርቅ የመሰለ፣ የትውልዱን ቤሄራዊ ስሜት የሰለበ  መሪ ሳይሆን መሪ  የሆነ እኩይ  ሰው ነበረ፡፡

ከአስራ ሰባት አመታት የትጥቅ ትግል በኋላ ብዙዎችን ያስከተለበትን የለውጥ እና የዴሞክራሲያዊ ሰርዓት ግንባታን ወደ ጎን በማለት በስልጣን የሚቆይበትን መንገድ በማመቻቸት እና የምህራባዊያንን ትኩረት በሚያገኝበት ስራ ላይ ተጠምዶ ዘመኑን አሳልፏል ፡፡ በስልጣን በቆየበት ግዚያት ሁሉ ከራሱ በላይ ማሰብ ተስኖት አገርና ህዝብን አስነብቷል፡፡

መለስ ዜናዊ በሰልጣን ዘመኑ እድሜ መጀመሪያ ጀምሮ ለመቀመጫው እንጂ ለአገርም ሆነ ለህዝብ ደንታ ስላልነበረው 80 ሚሊዮን ህዝብ ያለባትን አገር በፈቃዱ  ካለወደብ አሰቀርቷል፣ ህዝቡንም በዘርና

በሃይማኖት ከፋፍሎ ለዘመናት በመተሳሰብና በመከባበር በሰላም አብሮ የኖረን ህዝብ በጥላቻ እንዲተያይ በማድረግ አንዱ  በአንዱ ላይ ለማስነሳት እጅግ ዘግናኝ ጭፍጨፋዎችን በበደኖ፣ በአኝዋክ፣ እና በመሳሰሉት ከፍተኛ ግፍ ፈፅሟልም አስፈፅሟልም፡፡

ለይሰሙላ በህግ-መንግስት ላይ በተቀመጠው የዴሞክራሲ መብት መሰረት መደራጀት፣ ሀሳብን በነፃነት መግለፅ የሚሉ አንቀፆች ቢኖሩም ከወረቀት ያለፈ ትርጉም ስለሌላቸው መብታቸውን ተጠቅመ የሚደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ አባሎቻቸው እንዲሁም ሀሳቡን በነፃነት በመግለፅ  የህውሃት ቡድን የሚሰራውን  የሚቃወም በሙሉ የተለያየ ምክንያት እየተፈለገ ይታፈናል፣ ይታሰራል፣ ይገደላል፣ ደብዛው ይጠፋል፣ ይገረፋል በየማጎሪያ ካምፑ ማንም ጎብኝ በማያይበት ሁኔታ ዘመኑ እስኪያልፍ ይሰቃያል ገሚሱም  ከዚህ ሁሉ ጥቃት ለመሸሽ ይሰደዳል፡፡ ይህ ሁሉ የዜጎች ግፍና ሰቆቃ የተፈፀመው በዚሁ እድገትና ብልፅግና እንዲሁም ዴሞክራሲ  ከእኔ ወዲያ ላሳር ከሚለን  በዘረኛው በመለስ ነበር፡፡

ለሁለት አስርተ አመታት ብዙዎችን የገደለው፣ አገር የሸጠው እና በሃይል በህዝብ ጫንቃ ላይ የተጫነው መለስ ዜናዊና  ስርዓቱ በየግዜው ምክንያት እየፈለጉ እስር ቤት የጣሏቸው ንፁሃን ዜጎች ላይ ካለ እርህራሄ  ከእደሜ ልክ እስከ ሞት ቅጣት ይፈርዳል ያስፈርዳል፡፡

ይህንንና ተፅፈው የማያልቁ በደሎችን የፈፀመው እና ያስፈፀመው ዘረኛውና አመባገነኑ መለሰ ዜናዊ በስልጣን ዘመኑ ለሰራው ግፍ እና ላጥፋው ነብስ ፍትሃዊ በሆነ ስርሃት እንደ ሌሎች አመቦገነን ጓደኞቹ ቅጣቱን ሳይቀበል እና ለሌሎችም መማሪያ ሳያሆን ማለፉ የሚያበሳጭ ቢሆንም በግፍ የሞት ፍርድ እየፈረደ በየ ወህኒ ከወረወራቸው ንፁሃን ዜጎች መቅደሙ *ጉድጓዱን ስትቆፍር ብዙ አታርቀው የሚገባበት አይታወቅም እና* የሚለውን ብሂል አስታውሰኝ፡፡

እዛኛው መንደር ፈንግል ገብቷል፡፡ ፈንግሉ ከአውራዎቹ ጀምሯል ፡፡የኢትዮጲያን ህዝብ የዘመናት ሰቆቃ እና ዋይታችንን አንድዬ የሰማን ይመስላል፡፡ አምባገነኑ መለሰ ዜናዊም በጓደኞቹ ሲነገር የነበረውን የህክምና እረፍት እስከ ወዲያኛው አራዝሞት ላይመለስ ሄዱዋል፡፡

ሁሉም ነገር የመጨረሻ መጀመሪያ ላይ ደርሷል፡፡ መቃብር አፋፍ ላይ ያለን ስርዓት በተባበረ ክንድ የመጣያው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ልዩነታችንን አቻችለን አንድ ሆነን እንታገል፡፡

## ድል ለ ኢትዮጲያ ሕዝብ ሞት ለወያኔ!!

ለ አሰተያየት፡-ftih_lewegen@yahoo.com